ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት. ዴ. ፓ)
Tigray Democratic Party (T.D.P)

የህወሓት አመራር ሕግ አልበኝነትና መዘዙ

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ መግለጫ ሰኔ 30፣ 2012ዓም

የታዋቂው የመብት ታጋዩ አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ድንገተኛ ህልፈት ምንኛ እንዳሳዘነን እና ለመላ ቤተሰቡ እና አፍቃሪዎቹ መፅናናትን እንደተመኘን በተለያዩ ብዙሃን መገናኛ አውታሮች ስንገልፅ መሰንበታችን ይታወቃል።

የወንድማችን ሃጫሉ ፈት-ለፈት ገዳዮች ብቻ ሳይሆኑ ከበስተጀርባው ሁነው ግድያውን ያቀናበሩ፣ ያስታጠቁና አሁንም ተመሣሣይ ግድያ ለመፈፀም በረቀቀ ዘዴ እየዛቱ ያሉ ወንጀለኞች ሕግ ፊት ቀርበው በወንጀላቸው ልክ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ መንግሥትም ይሁን የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ እየጠየቅን እንገኛለን።

ለመሆኑ የዚህ ግድያ ዓላማ ምንድን ነው? አርቲስቱ ሃጫሉስ ምን በድሎ ነው በለጋ ዕድሜው የሚቀጨው? በሃጫሉ ግድያስ ሊደርስ የተፈለገው ግብ ምንድን ነው?!

እነዚህ ጥያቄዎችን በሰከነ መንፈስ ለመመለስ በምናሳላስልበት ጊዜ በሁሉም ምዕራፎች ብቅ የሚለው የህወሓት አመራር ነው!! ለምን?

አንድ ሁለት ዓመት ወደ ኋላ መለስ ብለን ከለውጡ ማግሥት ጀምሮ የተከሠቱትን ሁኔታዎች ስንመለከት፣ ለ27 ዓመታት ሥልጣን የቆየው የህወሓት አመራር በለውጡ ሂደት ተደናግጦ በአስገራሚ ሽሽት ላይ እንደነበረ ማንም ሠው የታዘበው ሐቅ ነበር። መቐለ መዳራሻው አድርጎ እዛው ከመሸገ በኋላ ፍርሃት ከወረረው ጭንቀቱ አገግሞ ወደ ነበረበት የሥልጣን ከፍታ ለመመለስ፣ ይሽንንም ካልቻለ ደግሞ የተገነጠለ የትግራይ መንግሥት መስርቶ እንደለመደው በሥልጣን ላይ ተቀምጦ የተካነበትን ሙስናና ብዝበዛ መቀጠል ነው።

ይሽን እኩይ ውጥን ለማሳካት የኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን ህገ-መንግሥቱ እንዲሁም ህገ-መንግሥታዊ ደንቡን ተከትሎ የተቋቋመው የፌደራል መንግሥት እንደማይፈቅድለት ጠንቅቆ ስለሚያውቀው ሌላ ዘዴ መተብተብ ነበረበት። ይሽ ዘዴ በሃገሪቱ ውስጥ እሱን የጣለው የህዝብ አመፅ በቀላሉ የሚከሰት መስሎት፣ ግርግር ቀስቅሶ የፌደራል መንግሥቱ አገርንና ህዝብን መምራት ወደማይችልበት ቅርቃር ውስጥ መክተትና ክፍተቱን እንዲሞላው ተፈላጊ ሆኖ እንዲገኝ ማድረግ ነው።

የህወሓት አመራር ለዚህ ዕቅድ ይረዳው ዘንድ በየክልሉ የፈጠራቸው አጋር ተብዬ ድርጅቶች ማሠማራትና በነሱ በኩል ስራ-አጡን ወጣት በማስታጠቅ፣ ለግብረ-ሽበራ በመቀስቀስ--አሰቃቂ ግድያና የንብረት ማውደም ዘመቻ ብሎም ህዝብን እርስበርስ የማባላትና አገርን የመበታተን ዘመቻ ማካሄድ ነው። ለዚህ ቅስቀሳ የሚረዱትም የሚድያ ተቋማትም እንደነ ድምፂ-ወያነና ትግራይ ቲቪ አሰማርቶ «ታጠቅ!» «ክተት!» እያለ ከርሟል።

በነዚህ መገናኛ ብዙሃን በኩል ሲለቀቅ የሰነበተው ስሜታዊ ልፈፋ፣ በትግራይ ህዝብ ላይ ያሣደረው የስነ-ልቦዊና ተፅእኖ በጣም ከባድ ነው። ከሁሉ የከበደውና ህዝቡን ያስጨነቀው ቅስቀሳ «በጠላት ተከበሃል እና ተነስ! መክት!!» የሚለው ነው። ይሽ ቅስቀሳ በተግባርም እንዲታይ እስከ 250 ሺ የሚያህል ወጣት

በሚሊሻና በልዩ ኃይል ወታደርነት አስታጥቆ ከዞን ወደ ዞን እያመላለሠ የህዝቡን ጭንቀት ጣራ እንዲነካ በማድረግ ላይ ይገኛል።

የህወሓት አመራር ችግሮችን በውይይት መፍታት የማይችል በራሡ ሽብርተኛ ለመሆኑ ከላይ እንደተጠቀሰው መገንዘብ ቢቻልም፤ ለዚሁ ተጨማሪ ማስረጃው በትግራይ ያሉትን እንደ ትዴፓ፣ ዓረናና ዓሲምባ የመሳሰሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዳይንቀሳቀሱ ማገድ ብቻ ሳይሆን አባሎቻቸውን «ባንዳ» «ከሃዲ» የሚል ሥም እየለጠፈ እንዲታሰሩ አልያም ከመኖሪያ ቄያቸው እንዲባረሩ እያደረገ ይገኛል። ከዚህ አልፎም በአሁኑ ወቅት ተቃዋሚ ያላቸውን የተፎካካሪ ፓርቲዎች አባላት ሥም ዝርዝር በየወረዳው እየለጠፈ በማሳደድ ላይ ይገኛል። የፓርቲያችን አመራር አባሎቻችን ወጣት ነጋሲ በላቸውን እና ወጣት ማርቆስ ፀጋይን ጨምሮ 15 አባሎቻችን ሰሞኑ ከየቤታቸው እየተለቀሙ ተወስደው አስርቤት ውስጥ እየማቀቁ ይገኛሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የህወሓት አመራር የኮሮና ወረርሽን ለመከላከል ጊዜያዊ አዋጅ አውጆ ሲያበቃ፣ ተላላፊ በሽታው መከላከሉን ዋጋ የሚያሳጣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እውቅና ያልሰጠው ምርጫ ማካሄድ አለብን ብሎ ሽርጉድ እያለ ይገኛል። ፩ኛ/ የህዝብ ጤንነት ነው የሚገደው ወይስ ሕገ-መንግሥቱን ያልተከተለ ምርጫ ማካሄድ?! ፪ኛ/ በዛ ላይ ደግሞ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን እያባረሩ፣ አባላቱን እያሰሩና እየደበደቡ ምን ዓይነት ምርጫ ሊባል ነው? ፫ኛ/ አሁንም የሚገርመው «በጠላት ተከበሃል! ክተት!!» እያሉ ጦርነትን እየቋመጡና ለእልቂት እየተዘጋጁ፣ ምርጫ ብሎ ህዝባዊ ተሳትፎ ግድ የሚል ሰላማዊ ክንዋኔ ይቻላል እንዴ? ለዚህ ሁሉ ጥያቄ የህወሓት አመራር መልስ የለውም ብቻ ሳይሆን፣ የጦርነት ክተት አዋጅና ምርጫ አብሮ ለማስኬድ መሞከር ወደ እብደት የተጠጋ ጭንቀት የወለደው ድርጊት እንደሆነ ይታየናል።

በመጨረሻም፣ ለተከበረው የትግራይ ህዝብ ልናስተላልፈው የሚገባ መልእክት ካለ፦

1. ትግራይ የኢትዮጵያ አካል ብቻ ሳይሆን እምብርትም ነው፤ ሊገነጡልህ የሚፈልጉ ቡድኖች ለግል ጥቅማቸውና ለሥልጣናቸው መሠንበት ሲሉ ስለሆነ «ወጊድ» በላቸው።

2. «ጠላት መጣብህ!» «ተከበሃል!» «ክተት!» እያሉ የሚቀሰቅሱህ አንተን መከታ አድርገው፣ እነሱ በሠላም ለመኖር አስልተው ነው። የመጣብህ ጠላት፣ የከበበህ አጥር የለም። ስለዚህ ከዘለአለም ወገንህ የሆነው የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሆነህ እነዚህ ሊያዳሙህ ያኮበኮቡትን ሙሠኞችና ስግብግም መሪዎች ወጊድ በላቸው።

የትግራይ ህዝብ ሆይ፣ መፃኢ ዕድልህ የተመሠረተው ከወገንህ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ ከነዚህ ሕገ-መንግሥት የማይገዛቸው፣ በረሃብ የሚቀጡህ አፋኝ መሪዎች ስላልሆነ ሠልፍህን ከህዝቡ ጋር አሳምረህ ተነሳ!!

ትዴፓ ምንግዜም ከጎንህ ነው!!